# ዜና አመዝኮ

ቅጽ 9 ቁጥር 11 ጥር፣ የካቲት 1996

**አ** የአደጋ
**መ** መከላከልና
**ዝ** ዝግጁነት
**ኮ** ኮሚሽን

## በዚህ ዕትም የሙስዋ ገጾች

- በ853 ወረዳዎች 21 ዙር የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ጥናቶች ተካሄዱ
- ለጥርና የካቲት ወራት 579 ሺህ ኩንታል በላይ የምግብ እርዳታ ተመደበ
- በዝግጁነት አቅም ላይ ያተኮረ ዓውደ ጥናት ተካሄደ
- በድርቅ ለተጎዱ ወገኖቻችን የገንዘብ እርዳታ ተለገሠ
- ለጋሾች 86 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር እርዳታ ለመስጠት ቃል ገቡ
- ህብረተሰቡ ለተረጂዎች የሚላከውን እርዳታ ለግል ጥቅማቸው የሚያውሉትን የማጋለጥ ተግባሩን ሊቀጥልበት እንደሚገባ ተገለፀ

*ዜና አመዝኮ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽንና ተባባሪዎቹ የሚያካሂዷቸውን የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት እንቅስቃሴዎችንና ሌሎች ተጓዳኝ ተግባራትንየሚዘግብ ወርሃዊ ልሣን ነው።*

*በአመዝኮ የሕዝብ ግንኙነት የተዘጋጀ*
☎ *52 92 59* ✉ *5686* *ፋክስ 514788*
*52 92 62*
**web.http// www. dppc.gov.et**

## በ853 ወረዳዎች በተደረጉ 21 ዙር የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ጥናቶች 465 ባለሙያዎች ተሳታፊ ሆነዋል::

ከ1994 ዓ.ም የበልግና የመኸር ዝናብ መጥፋት ጀምሮ እስከአለፈው ጥቅምት/ ሕዳር 1996 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ የአደጋ ክስተቶችን አስቀድሞ ለመተንበይ በተደረጉ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ጥናቶች በጠቅላላው በመላ ሀገሪቱ በሚገኙ 853 ወረዳዎች 21 ዙር ጥናቶች የተደረጉ ሲሆን በነዚህ ጥናቶችም ከ465 በላይ የሚሆኑ ባለሙያዎች ተሳታፊ መሆናቸውን የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መምሪያ ገለፀ::

ከመምሪያው የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው በተለይ በ1994/95 ዓ.ም የበልግና የመኸር ዝናብ መጥፋት ሳቢያ በሀገሪቱ ተከስቶ የነበረው መጠነ ሠፊ ድርቅ በተጠቂ ወገኖች ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ የመፍትሔ እርምጃዎችን ከወዲሁ ለማመላከት በመላ ሀገሪቱ በሚገኙ በርካታ ወረዳዎች ተደጋጋሚ መደበኛና አስቸኳይ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ጥናቶች ተካሂደዋል:: በተካሄዱት ጥናቶችም ሰብል አብቃይ በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች በ1994/95 ዓ.ም በተደረጉ ሠባት ዙር መደበኛና ፈጣን የመኸርና የበልግ ሰብል ግምገማዎች 561 ወረዳዎች የተሸፈኑ ሲሆን በነዚህ ጥናቶችም 354 ባለሙያዎች ተሳታፊ ሆነዋል::

በሌላ በኩልም በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ በአርብቶ አደሩ አካባቢዎች በተደረጉ 12 ዙር መደበኛና ፈጣን የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ጥናቶች 66 ወረዳዎች የተሸፈኑ ሲሆን በነዚህ ጥናቶችም 91 ባለሙያዎች ተሳታፊ መሆናቸውን ከመረጃው ለመገንዘብ ተችሏል:: ከነዚህም በተጨማሪ በ1994/95 ዓ.ም በተለያዩ በድርቁ ተጠቂ በሆኑ ወረዳዎች በርካታ የሥርዓተ ምግብ ጥናቶችና በአፋርና ሱማሌ ክልል በተከሰቱ የጎርፍ መጥለቅለቅ አደጋዎች ሳቢያ ሁለት የአስቸኳይ ጊዜ አደጋ ጥናቶች የተካሄዱ መሆኑን ከቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መምሪያ የተገኘው መረጃ ያመለክታል::

እነዚህ ጥናቶችም በአደጋ ተጠቂ የሆነው ሕዝብ ለከፋ ጉዳት ሳይጋለጥ በወቅቱ አስፈላጊው ዕርዳታ እንዲደርስለት ከመኖሪያ አካባበው እንዳይፈናቀልና ጥሪቱ እንዳይሟጠጥ ፣ በምግብ እጥረት ለተጎዱ እናቶችና ህፃናት ተገቢው ድጋፍ እንዲደረግ እና ለሰውና ለእንስሳት ጤና አስፈላጊው ድጋፍ እንዲቀርብ ለመንግሥትና ለረድኤት ድርጅቶች ተገቢውን የመፍትሔ እርምጃ በማመላከት እና እገዛ በማድረግ ከፍተኛ ውጤት ማስገኘታቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ መምሪያው የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሥርዓትን ለማጠናከር የተለያዩ እርምጃዎችን እየወሰደ መሆኑን አመልክቷል፡፡ በዚህ ረገድ መምሪያው የተለያዩ መንግሥታዊ መሥሪያ ቤቶችን ፣ የረድኤት ድርጀቶችን ፣ የተባበሩት መንግሥታት አካላትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጀቶችን በማሳተፍ እንደ መደበኛ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ጥናት መረጃ አተናተን ዘዴ ፣ የዕርዳታ ፍላጎት አተማመን የጥናት ዘዴ እና ፈጣን የአደጋ አጠናን ዘዴ የመሳሰሉ የተለያዩ የተሻሻሉ የአሠራር ዘዴዎችን በቅንጅት በማዘጋጀት ላይ ይገኛሉ፡፡

እንዲሁም መምሪያው የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መረጃ ጥራትን ለማሻሻል እና ቀልጣፋ፣ ፈጣንና ወቅታዊ የመረጃ ፍሰትን ለመዘርጋት የመረጃ ጥራት ቁጥጥር መምሪያን በማዘጋጀት እና የዋይድ ኤርያ ኔትወርክ ሥራ በሙከራ ደረጃ በማከናወን ላይ የሚገኝ መሆኑ ተገልጿል፡፡ በሌላ በኩልም መምሪያው በአርብቶ አደሩ አካባቢ ጠንካራ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሥርዓትን ለመዘርጋት በየደረጃው የሚገኙ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ባለሙያዎችን አቅም ለመገንባት ፣ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መረጃን በቀልጣፋ ሁኔታ ለማቀነባበርና ለመተንተን እና የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሥርዓትን በወረዳ ደረጃ ለማጠናከር የሚያስችሉ የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነ እንደሚገኝ ተመልክቷል፡፡

# ለጥር እና ለየካቲት ወራት ከ579 ሺህ ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ ተመደበ

ካለፈው ዓመት ድርቅ ሁኔታ ጋር በተያያዘና በዝናብ አለመስተካከል ሳቢያ በዚህ ዓመት በቂ ምርት ላላገኙና የምግብ እጥረት ላለባቸው ክልሎች ቀደም ሲል በተደረጉ ጥናቶች መሠረት በአውሮፓውያኑ አዲስ ዓመት ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች የምግብ ዕርዳታ የማቅረቡ እንቅስቃሴ ቀጥሏል።

በዚሁ መሠረት ለጥር እና የካቲት 1996 ዓ.ም የሚሆን ቀለብ ለሁሉም ክልሎች በጠቅላላው 579 ሺህ 271.4 ኩንታል ተመድቧል። ከዚሁ ከተመደበው የምግብ ዕርዳታ ውስጥም 438 ሺህ 590.4 ኩንታል መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ቀሪው 141 ሺህ 221 ኩንታል ደግሞ በአመዝኮ መመደቡንና 274 ሺህ 451 ኩንታል በጥር ወር 305 ሺህ 360 ኩንታል ደግሞ በየካቲት ወር 1996 ዓ.ም ለየክልሎች ተጓጉዞ ለተረጅ ወገኖች መከፋፈሉ ታውቋል።

ለየክልሎች የሚደረገው የዕርዳታ አመዳደብም በየክልሎቹ እንደሚገኘው ችግር ስፋትና ጥልቀት የሚለያይ ሲሆን በዚሁ መሠረት ለየወሩ ከተመደበው የምግብ ዕርዳታ ውስጥ ለየክልሎች የተሰራጨው በኩንታል በሚከተለው ሠንጠረዥ ቀርቧል።

| ክልል | ጥር | የካቲት | ድምር |
|---|---:|---:|---:|
| ትግራይ | 45881.5 | 79677 | 125588.5 |
| አፋር | 17590.6 | | 17590.6 |
| አማራ | 12668.4 | 12130 | 24798.4 |
| ኦሮሚያ | 21486.6 | 68761 | 90247.6 |
| ሱማሌ | 133670.3 | 63155 | 196825.3 |
| ደቡብ ሕዝቦች | 30653.1 | 66684 | 97337.1 |
| ድሬደዋ | 12500.9 | 13600 | 26100.9 |
| ጋምቤላ | | 1353 | 1353 |
| ድምር | 274451.4 | 305360 | 579811.4 |

## የዝግጁነት አቅምን ለማጠናከር በሚያስችሉ የተግባር ዕቅዶች ላይ ያተኮረ አውደ ጥናት ተካሔደ

በሀገራችን በተደጋጋሚ በመከሰት የሚታወቀውን የድርቅ አደጋ ስፋትና ጥልቀት አስቀድሞ ለመተንበይ እና አደጋው በተጠቂው ህብረተሰብ ላይ የከፋ ጉዳት ሳያደርስ አስቀድሞ የዝግጁነት አቅምን ለማጠናከር ለማስቻል በተዘጋጁ ተግባራዊ እቅዶች ላይ ያተኮረና በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን የአደጋ ጊዜ ምላሽ ችሎታ ማጠናከሪያ
ኘሮጀክት (SERA) የተዘጋጀ አውደ ጥናት የካቲት 22 ቀን 1996 ዓ.ም በኮሚሽኑ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ተካሂዷል::

በዚሁ ለአንድ ቀን በቆየ አውደ ጥናት መክፈቻ ላይ እንደተገለጸው በኮሚሽኑ የሚገኘው የአደጋ ጊዜ ምላሽ ችሎታ ማጠናከሪያ ኘሮጀክት የተቋቋመው የአደጋ ተጋላጭነት መሠረታዊ ምክንያቶችን በመለየት ለአደጋው ተጋላጭ የሆነውን ህብረተሰብ አቅም ለማጎልበትና የተለያዩ አደጋዎችን እንዲቋቋም ማስቻል ፣ እንዲሁም የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ አሠራርን በማጠናከር የሚከሰቱ የምግብ እጥረቶችን በተሻለ ሁኔታ ለማመላከትና የአደጋ ተጋላጭነትን መሠረታዊ ምክንያቶች ለመቅረፍ የሚያስችል አሠራር ለመዘርጋት ነው::

ኘሮጀክቱ ባለፉት ዓመታት በተከታታይ የምግብ ዕርዳታ በሚያገኙ አሥራ ስድስት ናሙና ወረዳዎች ያካሔደውን የአደጋ ተጋላጭነት ጥናት ኘሮ ፋይል መጠናቀቁና ይህም በቀጣይነት ለሚተገበረው የአደጋ ምላሽ አቅምና የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ ከፍተኛ እገዛ እንደሚያደርግ ተመልክቷል::

ይሁንና መንግሥት ችግሩን በዘላቂነት ለማስወገድ ለነደፈው የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ ስኬት አዲስ የምግብ ዋስትና ቅንጅት መፈጠሩ እና በዚሁ አማካይነትም ሴፍቲኔትና የመሳሰሉት እንደ አንድ የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ ለመተግበር መታቀዱ ፣

እንዲሁም የአመዝኮ ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል በወጣው አዋጅ መሠረት ከኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባር ጋር በማጣጣም የአደጋ ጊዜ ምላሽ አቅም ማጠናከሪያ ኘሮጀክትን ዓላማና ተግባራት እንደገና መከለሱ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ ከዚህ አኳያ የተዘጋጁት ተግባራዊ ዕቅዶች ለዐወደጥናቱ ተሳታፊዎች ውይይት መቅረባቸው ተገልጿል፡፡

በመሆኑም የአውደ ጥናቱ ዋና ዋና ዓላማም ከኘሮጀክቱ ተጠቃሚ ክልሎች ጋር በሚደረግ የጋራ የውይይት መድረክ ያለውን ግንኙነት የበለጠ ለማጠናከር እና በቀረበው የሥራ ዕቅድ ላይ በመወያየት አዳዲስ የሚታከሉ አስተያየቶችን በማካተት ሠነዱ የመጨረሻ መልክ እንዲኖረው ከስምምነት ለመድረስ ያለመ እንደሆነም ተብራርቷል፡፡

የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ኮሚሽነር ሲሞን መቻለ ዐውደጥናቱን ሲከፍቱ እንደተናገሩት አውደ ጥናቱ ያለፉ አሠራሮችን በመፈተሽ የኘሮጀክቱ የወደፊት የሥራ ዕቅዶች ሀገሪቱ ከምትከተለው የምግብ ዋስትና አቅጣጫ ጋር እንዲጣጣሙና ኮሚሽኑ የተጣለበትን አስቸኳይ አደጋዎችን የመከላከልና የመቋቋም ኃላፊነቱን ለመወጣት አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ለማስቻል ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል ብለዋል፡፡ አያይዘውም የዝግጁነት አቅምን የማጠናከር ኘሮጀክት የሀገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ ፣ በአነስተኛ ወጪ ግልፅና ውጤታማ መመሪያን በማካተት ከሚፈለገው ግብ ለመድረስ እንዲያስችል ታቅዶ የተዘጋጀ መሆኑን ጠቁመው ለዚህም ስኬታማነት የኘ ሮጀክቱ ተጠቃሚ ክልሎች ተሳትፎ ወሳኝነት ስላለው ሰነዱን በጥልቀት ፈትሸውና ተወያይተው ገንቢ ሃሳቦችን በማመንጨት የተግባራዊ ዕቅድ ሰነዱን ማጎልበት እንደሚጠበቅባቸው አሳስበዋል፡፡

የፌዴራል ፣ የአማራ ፣ የኦሮሚያ ፣ የደቡብና የትግራይ ክልሎች አደጋ መከላከልና ዝግጁነት የሥራ ኃላፊዎች ፣ የየክልሎቹ የምግብ ዋስትና ጽ/ቤት ኃላፊዎች የኘሮጀክቱ ባለሙያዎችና አማካሪዎች በተካፈሉበት በዚሁ ዐውደጥናት በጋራና በቡድን በመሆን ሰነዱን በጥልቀት በመመርመር ለተግባራዊነቱ የሚበጁ ሃሳቦችን በማመንጨት ስብሰባው ተጠናቅቋል፡፡

## *በድርቁ ሳቢያ ለምግብ እጥረት ለተጋለጡ ወገኖቻችን የገንዘብ ዕርዳታ ተለገሠ*

በድርቁ ሳቢያ ለምግብ እጥረት የተጋለጡ ወገኖቻችንን ለመደገፍ በሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር ያሉ የተለያዩ የህብረተሰቡ ክፍሎች የሚያደርጉት የገንዘብ ዕርዳታ አሁንም እንደቀጠለ ነው፡፡

በዚሁ መሠረት ከታህሳስ ወር 1996 ዓ.ም አጋማሽ ጀምሮ እስከ የካቲት 16 ቀን 1996 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ ወስጥ ከሀገር ውስጥ በጠቅላላው ብር 246 ሺህ 767 ከ95 ሳንቲም እና በውጭ ሀገር ከሚኖሩ ኢትዮጵየውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች ደግሞ 27 ሺህ 843.30 የአሜሪካን ዶላር፣ 7 ሺህ ዩሮ እና 2 ሺህ 850 የስዊስ ፍራንክ ተለግሰል፡

ዕርዳታውን ከለገሡት መካከልም በጃፓን ሀገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች 22,983.30 የአሜሪካን ዶላር፣ በኔዘርላንድ ሀገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን 7,000.00 ዩሮ ፣ በቻይና ቤጂንግ ኗሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች 4,86000 የአሜሪካን ዶላር ፣ በተባበሩት መንግሥታት የኢትዮጵያ ቋሚ መልዕክተኛ ጽ/ቤት 2,850.00 የስዊስ ፍራንስ ፣ የኢትዮጵያ ፈንጅ አምካኝ ጽ/ቤት ሠራተኞችና አመራር 117,276.41 ብር ፣ ሠላም የጭነት ማመላለሻ ባለንብረቶች ማህበር 36,802.25 ብር፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር 21,229.74 ብር፣ በስቴዲየም ዙሪያ የቴብል ቴኒስና የጆተኒ ማጫዎቻ ባለንብረቶች 300.00 ብር፣ የለገሱ ሲሆን ሌሎችም ከብር 197 እስከ ብር 14 ሺህ ድረስ መለገሳቸውን ከፋይናንስ አገልግሎት የተገኘው መረጃ አመልክቷል፡፡

በአጠቃላይ ከድርቁ መከሰት ማግስት ጀምሮ እስከ የካቲት ወር 1996 ዓ.ም መጀመሪያ ድረስ በድርቁ ሳቢየ ለተጎዱ ወገኖቻችን መርጃ በድምሩ ከ102 ሚሊዮን ብር በላይ በጥሬ ገንዘብ ዕርዳታ ተገኝቷል፡፡

ከዚህ ወስጥ ብር 89 ሚሊዮን 924 ሺህ 753 ከ16 ሳንቲም፣ ከሀገር ውስጥ ከማዕከልና ከክልሎች ከተለየዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የተለገሰ ሲሆን፣ በውጭ ሀገር ከሚኖሩ ኢትዮጵየውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች ደግሞ 497 ሺህ 33 ከ83 የአሜሪካ ዶላር፣ 97 ሺህ 574 ከ34 ዩሮ፣ 45 ሺህ 300 የስዊስ ፍራንክ እና 8 ሚሊዮን 104 ሺህ 200 የጅቡቲ ፍራንክ በጥሬ ገንዘብ ተለግሷል። ቀሪው ደግሞ ግምታቸው ብር 4 ሚሊዮን በሚሆን የቁሳቁስ ዕርዳታ በዓይነት የተለገሠ መሆኑ ታውቋል፡ ከዚሁ በጥሬ ገንዘብ ከተገኘው ዕርዳታ ውስጥም በአብዛኛው ለሕፃናትና እናቶች አልሚ ምግብ መግዣ፣ ጥሪታቸው ለተሚጠጠባቸው አርሶ አደሮች የዘር አቅርቦት፣ ለእንስሳት ጤና ክብካቤ መድኃኒት መግዣና ለዕርዳታ እህል አቅርቦት መጓጓዣ በማዋል የድርቁን አደጋ በመቋቋሙ ጥረት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡

## ለጋሾች 86 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ዕርዳታ ለመስጠት ቃል ገቡ

❖ *በወቅቱ ሁኔታ ላይ የተካረ ውይይት ተካሄደ*

*በያዝነው የፈረንጆች ዓመት ኮሚሽኑ ላቀረበው የእርዳታ ጥየቄ የዩናይትድ ስቴትስና የእንግሊዝ መንግሥታት 86 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ቃል መግባታቸው ተገለፀ።*

ይህ የተገለፀው በሀገሪቱ የሚገኘውን የድርቅ ሁኔታና ችግሩን ለመቋቋም የምግብና ምግብ ነክ የልሆኑ ፍላጎት አቅርቦት የሚገኝበትን ደረጃ ለመገምገም የለጋሽ መንግሥተት አምባሳደሮች፣ የተባበሩት መንግሥተት ልዩ አካላት፣ የሥራ ኃላፊዎችና ተወካዮች በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን የመሰብሰቢያ አዳራሽ የካቲት 5 ቀን 1996 ዓ.ም ባካሄዱት የምክክር ስብሰባ ላይ ነው፡ ከዚሁ ቃል ከተገባው ዕርዳታ ውስጥ የዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት 62 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የሚገመት 156 ሺህ 260 ሜትሪክ ቶን የምግብ ዕርዳታ፣ 6 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ደግሞ ምግብ ነክ ላላሆኑ አቅርቦቶች በድምሩ 68 ሚሊዮን ዶላር መለገሱ ታውቋል።

የእንግሊዝ መንግሥት በበኩሉ ቃል ከገባው 18 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ውስጥ ለሥርዓተ ምግብ፣ ለጤናና ለውሃ አቅርቦት 9 ሚሊዮን ዶላር፣ የሀገር ውስጥ እህል ግዥን ጨምሮ ለምግብ ዕርዳታ እንዲውል 9 ሚሊዮን ዶላር መድቧል:: በተመሳሳይም ቀደም ሲል የካናዳ መንግሥት 3.1 ሚሊዮን የካናዳ ዶላር ለመለገስ መወሰኑም ታውቋል::

የአመዝኮ ኮሚሽነር ሲሞን መቻለ በዚሁ በወቅቱ በሀገሪቱ የምግብ ዕርዳታ ፍላጎት ዙሪያ ባተኮረው የምክክር ስብሰባ ላይ እንደተናገሩት በየጊዜው ድርቅ በሚያስከትለው ተጽዕኖና ሥር ከሰደደው ድህነት ጋር በተያያዘ የሚከሰተውን የምግብ እጥረት ለዘለቄተው ለመፍታት መንግሥት የነደፈው የምግብ ዋስትና ኘሮግራም ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እስከሚሆን ድረስ በአሁኑ ወቅት ያለው የምግብ አቅርቦት ኘሮግራም ይቀጥላል::

ኮሚሽነሩ አያይዘውም በአርብቶ አደሩ አካባቢ በተለይም በሱማሌ ክልል በቅርቡ በተካሄደው አጠቃላይ ሁኔታዎች ግምገማ ውጤት ኮሚሽኑ በታህሳስ ወር ይፋ ካደረገው የዕርዳታ ጥያቄ ፍላጎትና ትንበያ ጋር ተቀራራቢነት እንዳለው አብራርተዋል::

በያዝነው ዓመት ከምግብ ዕርዳታው በተጨማሪ ምግብ ነክ ያልሆኑ ፍላጎቶች ማለትም የሥርዓተ ምግብ፣ የጤና፣ የውሃ፣ የዘር አቅርቦቶችና የአቅም ግንባታ ፍላጎቶች ካለፈው ዓመት በበለጠ ሁኔታ ትኩረት እንደሚሹ ያመለከቱት ኮሚሽነሩ ለጋሾች ለእነዚህ አቅርቦቶች መሟላት ከፍተኛ ግምት በመስጠት ተገቢወን ድጋፍ እንዲያደርጉ ጠይቀዋል::

በዚሁ የምክክር ስብሰባ ላይ ከድርቁ ጋር በተያያዘ ለሚባባሱ የወባና መሰል የወረርሽን በሽታዎችን ለመከላከል የመድኃኒትና የተጓዳኝ አገልግሎቶች አቅርቦት፣ በህፃናት ላይ የሚከሰተውን የምግብ እጥረት ለመቋቋም የጤናና የተመጣጠነ ምግብ አቅርቦት፣ እንዲሁም ድርቅ በሚከሰትባቸው በአንዳንድ አካባቢዎች ለሚማሩ ተማሪዎች የምገባ ጣቢያ አገልግለቶች ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው ተጠቁሟል::

ባለፈው ዓመት የድርቅ አደጋ በተከሰተባቸው ቦታዎች ሰብል ሙሉ በሙሉ በመውደሙ ለጥሪት አልባነት የተዳረገው አርሶ አደር ዛሬም ከዚህ ተደራራቢ ችግር ወጥቶ ገና ያላገገመ በመሆኑ የአስቸኳይ እርዳታ አቅርቦቱ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ያሳሰቡት ኮሚሽነር ሲሞን ለተጎጂ ወገኖች ዕርዳታውን ቀጣይነት ባለውና በተሟላ መልኩ ለማቅረብ ባለፈው ዓመት ቃል ተገብቶ የዘገየውን ዕርዳታ በመላክና ዘንድሮ ለተጠየቀውም ምላሽ በመስጠት ለጋሾች እንደወትሮው ሁሉ እንዲተባበሩ ጠይቀዋል።

በዚህ ወቅትም ለጋሾችና የድርጅቶች ተወካዮች የተከሰተው የምግብ እጥረት ችግርና ድርቁ ያስከተለው ተፅዕኖ ሙሉ በሙሉ እስኪቀረፍ ድረስ ለተረጂው ሕዝብ የሚፈለገውን ዕርዳታ በቀጣይነት ለመለገስ እንደሚጥሩ ገልፀዋል።

## ህብረተሰቡ ለተረጂዎች የሚላከውን ዕርዳታ ለግል ጥቅማቸው የሚያውሉትን የማጋለጥ ትብብሩን አጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል

የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ባለፈው ዓመት በተከሰተው ድርቅ ለምግብ እጥረት ለተጋለጡ ወገኖች የተላከውን የዕርዳታ እህል ወደ ዕርዳታ ማደያ ጣቢያ አላደረሱም በተባሉ አጓጓዦች ላይ ክትትልና ማጣራት አድርጎ ጉዳዩ ወደ ህግ የሚቀርብበትን ሁኔታ በማመቻቸት ላይ እንደሚገኝ አስታወቀ። ህብረተሰቡም ለተረጂ ወገኖች የሚላከውን ዕርዳታ ለግል ጥቅማቸው የሚያውሉትን የማጋለጥ ትብብሩን አጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪ አቀረበ።

ኮሚሽኑ ለመገናኛ ብዙሃን ባሰራጨው በዚሁ መግለጫው በ1994/95 ዓ.ም በመላ ሀገሪቱ ተከስቶ የነበረውን ድርቅ መንግሥት ፣ ህዝብና ዓለም አቀፍ ለጋሾች ባደረጉ ርብርብ አደጋው የከፋ ጉዳት ሳያደርስ ለመከላከል ተችሏል።

ይኸን በሀገሪቱ የድርቅ ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ አሳሳቢ የነበረውን ችግር ለመቋቋም መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ከዕለት ጉርሱ በመቀነስ ወገኑን ለመታደግ ያሳየው ጥልቅ ወገናዊ ስሜትና ቁርጠኝነት በዓለም አቀፍ ለጋሾችና የውጭ መገናኛ ብዙሀን ጭምር የብዙዎችን አድናቆት ማትረፉ ኢትዮጵያዊነት የቤተሰብ የመደጋገፍና የወገን አለኝታነት መገለጫ መሆኑንም በውል አመልክቷል ብሏል።

ይሁን እንጂ አደጋውን በመከላከልና ለተረጂው ህዝብ አስፈላጊውን ሰብዓዊ ዕርዳታ በማድረስ የወገኖቻችንን ሕይወት ለመታደግ በተደረገው የተቀናጀ እንቅስቃሴ ሂደት ቅንጣት ታህል የሰብዓዊነት ስሜት በሌላቸው በአንዳንድ የግል ጥቅም ፈላጊዎች ሳቢያ አልፎ አልፎ የዕርዳታ እህል በማድረስና በማከፋፈል ሂደት ችግሮች መከሰታቸውን አስታውቋል። ከእነዚህ ችግሮች ወስጥም አንዱ ኮሚሽኑ በተገቢው መንገድ እንዲያጓጉዙና ለተረጂው እንዲደርሱ ኃላፊነት የሰጣቸው አንዳንድ ክፍሎች የዕርዳታ እህልን ለብክነትና ለግል ጥቅም ማዋላቸው እንደሆነም አብራርቷል።

ኮሚሽኑ በመግለጫው ላይ እንዳመለከተው በተለያዩ ጊዜያት ከናዝሬትና ከኮምበልቻ ማዕከላዊ መጋዘኖች ወጪ በማድረግ በገቡት ውል መሠረት ለአፋርና ለሱማሌ ክልሎች ዕደላ ጣቢያዎች እንዲያደርሱ የተረከቡትን የዕርዳታ እህል አጓጓዥ ድርጅቶቹ በግለሰብ መጋዘን ማራገፋቸው ስለተደረሰበት ተገቢው ምርመራና ማጣራት ተደርጎ በፌዴራል ፖሊስ ወንጀል ምርመራ መምሪያ የወንጀል ክስ ተመስርቶ በመጣራት ላይ ይገኛል።

አጓጓዥ ድርጅቶቹ በአፋር ክልል ለሚገኙ ተረጂዎች ቴሩ አውላሎና በረሃሌ የዕርዳታ ማደያ ጣቢያዎች ለተረጂው ወገን እንዲደርሱ የተረከቡትን እህል በመቀነስ ከተራበ ሕዝብ ጉሮሮ ነጥቆ ለመክበር ያደረጉት ሙከራ ሰብዓዊነት የጎደለው ተግባር በመሆኑ ሊኮነንና ሊወገዝ እንደሚገባ መግለጫው አሳስቧል። ከኮምበልቻ ማዕከላዊ መጋዘን በ17/8/95 እና በ23/8/95 ዓ.ም የጫኑትን እህልና አልሚ ምግብ በውሉ መሠረት ወስደው ማስረከብ ሲገባቸው በግለሰብ መጋዘን በማራገፍ ህጋዊ አሠራርን ያልተከተለ ደረሰኝ ማቅረባቸው እንደተደረሰበትም አመልክቷል።

በዚህ የወንጀል ክስ ጉዳይ በመጣራት ላይ የሚገኘው አንደኛው አጓጓዥ ድርጅት ከኮምበልቻ ማዕከላዊ መጋዘን ለአፋር ክልል ተረጂዎች እንዲደርስ በ23/8/95 ዓ.ም በሁለት መኪኖች አልሚ ምግብ ጭኖ የወጣ ቢሆንም ሁለቱ መኪኖች በአንድ ቀን ልዩነት በመመለሳቸው በኮሚሽኑ የኮምበልቻ ማዕከላዊ መጋዘን ሠራተኞች ዘንድ ባስከተለው ጥርጣሬ አማካይነት ለፖሊስ በተደረገው ጥቆማ ሊደረስበት መቻሉ ታውቋል።

በሌላ በኩል ኮሚሽኑ በጥቅምት ወር 1995 ዓ.ም ከናዝሬት ማዕከላዊ መጋዘን ወጪ በማድረግ በሶማሌ ክልል አፍዴር ዞን ለሚገኙ ተረጂ ወገኖች የተላከውን የዕርዳታ እህል በባሌ ዞን በሶፍ ዑመር ከተማ በግለሰብ መጋዘን ውስጥ ተራግፎ ለአንድ ዓመት ያህል ከቆየ በኋላ የአካባቢው ህብረተሰብ ለመስክ ሥራ ለተንቀሳቀሱ የኮሚሽኑ የኦዲትና ኢንስፔክሽን ባለሙያዎች ባደረገው ጥቆማ ሊደረስበት መቻሉን መግለጫው አብራርቷል። እያይዞም ጉዳዩ በኮሚሽኑ የኦዲትና ኢንስፔክሽን አገልግሎት ተጨማሪ ክትትል እየተደረገበት ሲሆን ቀደም ሲል በተደረገው ማጣራትም እህሉ ለአንድ ዓመት ያህል ተቀምጦ ለብልሽት መዳረጉ መረጋገጡንና አስፈላጊው ምርመራ በማካሄድ ለህግ ለማቅረብ በመንቀሳቀስ ላይ እንደሚገኝ አስታውቋል።

ይህ ዓይነቱ ችግር በ1992 ዓ.ም በሶማሌ ክልል አስከፊ ድርቅ ደርሶ በነበረበት ወቅት ለአፍዴር ዞን የተላከው የምግብ ዕርዳታ በባሌ ዞን ጊኒር ላይ ተራግፎ በመገኘቱ ኮሚሽኑ ባደረገው ያላሰለሰ ክትትል ለችግሩ ተጠያቂ የሆኑትን አጓጓዥ ድርጅቶች ለህግ አቅርቦ የክሱ ሂደት በመታየት ላይ እንደሚገኝ መግለጫው አስታውሷል።

በተረጂው ህዝብ ላይ የተፈፀሙትን እነዚህን ወንጀሎች በማጣራት አጥፊዎቹን ለህግ ለማቅረብ አስፈላጊው ምርመራና ክትትል በማድረጉ ሂደት ህብረተሰቡ በጥቆማ በማጋለጥ ያሳየው ትብብር በአርአያነት የሚጠቀስ ነው ብሏል፡ በቀጣይም ሕብረተሰቡም መንግሥት የድርቁን አደጋ ለመቋቋም እያደረገ ያለውን ያልተቆጠበ ጥረት በማደናቀፍና የአያሌ ተጎጂ ወገኖቻችንን ሕይወት አደጋ ላይ በመጣል የዕርዳታውን እህል ለግል ጥቅማቸው በማዋል ሰብዓዊነት የጎደለው አስነዋሪ ተግባር ለመፈጸም የሚሞክሩ ወገኖችን በማጋለጥ ለህግ እንዲቀርቡ የተለመደ ትብብሩን እንዲቀጥል ኮሚሽኑ ባሰራጨው መግለጫ ጥሪ አቅርቧል።